ሜሪላንድ ትራንስፖርት
ክፍል

# ርዕስ 6 አቤቱታ መመሪያ

ማንኛውም ሰው በሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል በዘር፣ ቀለም፣ ወይም ትውልድ መነሻ የተነሳ መድልዎ ደርሶብኛል ብሎ የሚያምን ከሆነ የቢሮውን ርዕስ 6 አቤቱታ ቅጽ ሞልቶ በመላክ ርዕስ 6 አቤቱታ ማስገባት ይችላል። የሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል አቤቱታዎችን ከተቀበለ በሁዋላ ከ 180 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይመረምራል። የሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል የሚያየው የተሟሉ አቤቱታዎችን ነው።

አቤቱታውን እንደተቀበልን፣ የሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል ጉዳዩን በማየት ቢሮአችን ስልጣን እንዳለው ያረጋግጣል። አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታው በቢሯችን እንደሚመረመር የሚያስታውቅ ደብዳቤ ይደርሰዋል።

የሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል አቤቱታውን ለመመርመር 60 ቀናት አለው። ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገ፣ የሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል አቤቱታ አቅራቢውን ሊያነጋግር ይችላል። አቤቱታ አቅራቢው ደብዳቤው ከተጻፈበት ጀምሮ የተጠየቀውን መረጃ ለጉዳዩ ለተሰየመው መርማሪ ለመላክ 15 ቀናት አለው። መርማሪውን አቤቱታ አቅራቢው ካላገኘው ወይም ተጨማሪውን መረጃ በ 15 ቀናት ውስጥ ካላገኘ፣ የሜሪላንድ ትራንስፖርት ክፍል ጉዳዩን ሊዘጋው ይችላል። አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን ማስቀጠል ካልፈለገ፣ ጉዳዩ ሊዘጋ ይችላል።.

መርማሪው አቤቱታውን ከመረመረ በሁዋላ፣ ለአቤቱታ አቅራቢው ከሁለቱ አንዱን ደብዳቤ ያቀርባል፥ የመዝጊያ ደብዳቤ ወይም የግኝት ደብዳቤ (ኤልኦኤፍ)። የመዝጊያ ደብዳቤ ክሶቹን በማጠቃለል የርዕስ 6 ጥሰት አለመድረሱን እና ጉዳዩ መዘጋቱን ያሳውቃል። ኤልኦኤፍ የክሱን ሁኔታ እና የተደረጉትን ቃለ መጠይቆች በአጭሩ የሚያቀርብ ሲሆን ከዚም የዲሲፕሊን እርምጃ፣ የሰራተኛ ተጨማሪ ስልጠና ወይም ሌላ ተግባር ይወስዳል። አቤቱታ አቅራቢው ውሳኔውን ይግባኝ ማለት ከፈለገ፣ የመዝጊያው ደብዳቤ ወይም የኤልኦኤፉ የጽሁፍ ጥያቄ በመዝጊያው ደብዳቤ ወይም በኤልኦኤፍ እንደተጠቀሰው ለሜሪላንድ ትራንስፖርት ዲፓርትመንት ጸሀፊ ወይም ለተወካዩ 10 ቀናት አለው።

ማንኛውም ሰው አቤቱታውን በቀጥታ ለፌዴራል ትራንዚት አስተዳደር፣ FTA Office of Civil Rights, 1200 New Jersey Avenue SE, Washington, DC 20590 ማስገባት ይችላል።

መረጃ በሌላ ቋንቋ ከተፈለገ፣ ሽራይበር ትራንስሌሽን ኢንክን (Schreiber Translations, Inc.) በ1-800-822-3213፣ ወይም አድ-አስትራን (Ad-Astra) በ301-408-4242 ወይም 1-800-308-4807 ያግኙ።